# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 18 ቀን 2005 ዓ.ም**

**መከላከያ ውስጥ የወያኔ ሹመኞች እርስ በርስ እየታመሱ መሆኑ ተጠቆመ፤**

**የአየር ኃይል ዋና አዛዥ ተብየው ሞላ ኃይለማርያም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከሳሞራ የኑስ ተሰጠው ተባለ፤**

**የብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ዋና አዛዡ ክንፈ ዳኘው ላልተወሰነ ግዜ መንሳፈፉ ተገለጠ፤**

**በዘመቻ ጥረግ ተብሎ ስያሜ በወጣለት እፈሳ 56 ባለስልጣናትና ባለሀብቶች ታሰሩ፤**

**የአዜብ መስፍን እጣ ፈንታም አልለየለትም ተባለ፤**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የሀገር እና የህዝብ ገንዘብ በከፍተኛ ሁኔታ እየተመዘበረ ነው ብሎ ሪፖርት ካቀረበ ወዲህ በወያኔ የመከላከያ ሚኒስተር ከፍተኛ መኮንኖች መሀከል ትርምስ መፈጠር የጀመረ መሆኑ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ከተገኘው ዜና ማወቅ ተችሏል::

ባሳለፍነው ሳምንት በጦር ኃይሎች አቅራቢያ በሚገኘው መኮንኖች ክበብ ውስጥ በተደረገ ግምገማ መሰረት የመምሪያ ኃላፊ የሆኑ የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸውና ጄኔራል ተብየዎች የተገኙ ሲሆን በዚሁ ግምገማ ላይ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱን መስጢር አሳልፋችሁ እየሰጣችሁ ወንጀለኛ ናችሁ እያስባለችሁን ነው በማለት የኃይለማርያም ደሳለኝን የጦር ኃይሎች አዛዥነት ስልጣን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው ሳሞራ የኑስ ሲያስፈራራና ሲሳደብ እንደነበረ ምንጮቹ ገልፀዋል::

በኦዲተር ተጠንቶ 4 ቢሊዮን ብር አጥፍቶዋል ተብሎ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት በመቅረቡ የተደናገጠው ሳሞራ በየአቅጣጫው ከፍተኛ ባለስልጣናት ማስተባበያ እንዲሰጡ እያስደረገ ቢሆንም በህወሀት መሀከል በተፈጠረው ክፍፍል ምክንያት አንዱን ቡድን ለመፈንቀል

እና በሙስና ከስሶ ወደ ዘብጥያ ለማውረድ በሚደረግ ፋክቻ የተነሳ መከላከያ እየታመሰ እንደሚገኝ ምንጮቹ ገልፀዋል።

ይህንኑ ክፍተት ለመድፈን ሲባል የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ለሰባት ቀናት የፈጀ ግምገማ ያደረጉ ሲሆን ጉዳዩ እየከረረ በመምጣቱ ላልተወሰነ ግዜ እንዲቋዋረጥ የተደረገ ቢሆንም ሳሞራ ግን ውስጥ ውስጡን አንዳንዶቹን እያባረረ እና እየሾመ እንደሚገኝ ተጠቁሞዋል።

ከዚህ ቀደም ታግዶ ለተመለሰው .....ለአየር ኃይል ዋና አዛዥ ለሆነው ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማርያም ጥብቅ እና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንደሰጠው ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

በቅርቡ ወደ ሀገር ውስጥ ይገባሉ ተብሎ ከሚጠበቁት የሩሲያ ከፍተኛ መኮንኖች መሀከል ቅደሚያ የሚቆጣጠሩት የአየር ኃይሉን እንደሆነ ምንጮቹ ጠቁመው በተለይ ጄ/ል ሞላ ኃይለማያም ከጄ/ል ሳሞራ ጋር እሳት እና ጭድ የሆነበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ነገሮች እንዲከረሩ እና በመኮንኖቹ መሀከል ውጥረቱ እንዲባባስ አድርጎታል ተብሎዋል።

በዚሁ በመከላከያ ጄኔራል መኮንኖች መሀከል በተነሳ ትርምስ እና ሽኩቻ ምክንያት ቁጥራቸው የበዙ የመምሪያ ኃላፊ የሆኑ ጄኔራሎች በግዳጅ የዓመት እረፍት በሚል ላልተወሰነ ግዜ ከስራ ገበታቸው ላይ በሳሞራ የኑስ ፊርማ እየታገዱ ሲሆን የመለስ ቀኝ እጅ ሆኖ ሹመት ያገኘው ጄኔራል ክንፈ ዳኘው የተባለውም ከነዚህ መሀከል አንዱ እንደሆነ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ገልጾዋል።

በህወሀት ነባር ባለስልጣናት መሀከል የተፈጠረው ንትርክ እና ሽኩቻ በኩርፊያ ላይ ያስቀራቸው ቢሆንም ወደ መከላከያ ጄኔራሎች ዘልቆ በቡድን ተከፋፍለው አንዱ አንዱን በጎሪጥ የሚመለከትበት ደረጃ ላይ ባለበት በዚህ ወቅት ሳሞራ በእረፍት ስም እያነሳቸው እንደሚገኝ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል።

በመከላከያ ስር የኢንጅነሪንግ እና ብረታ ብረት ኮርፖሬሽን ዋና አዛዥ ሆኖ በመለስ ሹመት የተሰጠው የአድዋው ተወላጅ ብ/ጄ/ል ተብየው ክንፈ ለእረፍት በሚል ላልተወሰነ ግዜ እንደታገደ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልጾ በአሁኑ ሰዓት ለግዜው ተብሎ ሌላ አንድ የወያኔ አባል ጄኔራል ተብየው ቦታውን እንደተቆጣጠረም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በሀገሪቱ ትልልቅ ፋብሪካዎችንና የመኪና መገጣጠሚያዎችን አቋቋሞ የጄኔራል ተብየ መኮንኖችን ኪስ ማደለቢያ የሆነው ይሄው የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር የሀገር እና የህዝብ ሀብት ማውደሙን የኦዲተር መስሪያ ቤት በይፋ ያጋለጠው መሆኑ አይዘነጋም።

በክንፈ ዳኘው ሲመራ የቆየው ይሄው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በስሩ ባሉት መምሪያ ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ተመድበው ሲሰሩ የቆዩት እውቀት እና ችሎታ የሌላቸው ከበረሀ የመጡ የህወሀት መኮንኖች በመሆናቸው ብዙ የተማሩ ሰዎች መስሪያ ቤቱን ለቅቀው በመውጣት ባዶ ማስቀረታቸውን ተከትሎ ኮርፖሬሽኑ የሚጠበቅበትን ያህል ለመስራት አለመቻሉንም ምንጮቹ ጠቁመዋል።

በዚሁ በመከላከያ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን መስሪያ ቤት ውስጥ የተማሩና እውቀት ያላቸው መሀንዲሶች ሳይቀር በተራ ስራ ላይ ተመድበው የሚገኙ ሲሆን ከላይ የመምሪያ ኃላፊ ሆነው የተቀመጡት በረሀ የነበሩት የወያኔ አባላት ስራ ለማሰራትም ሆነ ለመስራት ብቃት እና ችሎታ ስለሌላቸው አብዛኛዎቹ ሙያተኞች እየለቀቁ በመውጣት ኮርፖሬሽኑን ባዶ እያስቀሩት መሆኑንም ምንጮቹ ጠቁመዋል::

ለምሳ አበል ብቻ አራት እና አምስት መኮንኖች ሆነው ከ70 ሺህ ብር በላይ እንደ ቀልድ እያወጡ የሚዝናኑት እነዚሁ የቀድሞ የወያኔ ታጋዮች የአሁኑ የመከላከያ መኮንኖች በሀገር እና በህዝብ ገንዘብ እየቀለዱ ያሉት ክንፈ ዳኘው ባመቻቸላቸው መንገድ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

አንዳንድ ግምቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በአሁኑ ሰዓት ከስራው የታገደው ክንፈ ዳኘው በሳሞራ የኑስ ፊርማ በመሆኑ ግለሰቡን በሙስና ለመክሰስ አስበው ሳይሆን አይቀርም በማለት እየተወራ ይገኛል::ይህንኑ ተከትሎ በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን መስሪያ ቤት ውስጥ ትርምስ በመፈጠሩ አንዱ አንዱን ለማድመጥ ፍቃደኛ ያልሆኑበት ደረጃ ላይ መደረሱንም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በ ክንፈ ዳኘው ምትክ ለግዜው ተብሎ የተቀመጠው ጄኔራል ተብየው መኮንን የኮርፖሬሽኑን የሂሳብ አያያዝ ለማጣራት አንድ ኮሚቴ አቋዋቁሞ በመስራት ላይ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ማን አይዞህ እንዳለው ባይታወቅም የወያኔው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ የፌዴራል ኦዲተር መስሪያ ቤት ያቀረበውን ሪፖርት ተከትሎ የአራት ሚኒስትር መስሪያ ቤት ኃላፊዎችን ጠርቶ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ከነዚህ መሀከልም አንደኛው የመከላከያ ሚኒስትር መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል::

አባዱላ ገመዳ በዚሁ በጠራው ስብሰባ ላይ እንዳለው ከሆነ በየግዜው የእናንተን ተመሳሳይ ሪፖርት ለመስማት ፍቃደኛ አይደለንም ...የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባቀረበው ሪፖርት መሰረት አንድ ኮሚቴ ተቋዋቁሞ በደንብ ከተጣራ በሁዋላ ዝርክርክ አሰራር ሲከተሉ የነበሩ የስራ ኃላፊዎች ይባረራሉ እንደ አስፈላጊነቱም ይታሰራሉ በማለት በልበ ሙሉነት ሲያስጠነቅቅ መዋሉ ታውቋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በወያኔ ቡድን ውስጥ በተፈጠረ ክፍፍል የተነሳ ውጥረቱን ለማርገብና የአንደኛውን ወገን ለማስደንገጥ በሙስና ሰበብ ተጠርጥረው ዘብጥያ ከወረዱት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ከመላኩ ፈንታና ከምክትሉ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ በሁዋላ እየተያዙ ያሉት ባለስልጣናት ቁጥር መጨመሩ ታወቀ::

ዘመቻ ጥረግ ተብሎ ስያሜ በወጣለት በዚሁ የአፈሳ እስራት 56 ሰዎች ለእስር የተዳረጉ ሲሆን ሰሞኑን የሚሌ .....የሞያሌ ......የናዝሬት.....ጉምሩክ ስራ አስኪያጆችን እንዲሁም ሌሎች የመምሪያ ኃላፊዎችን... ባለሀብቶችንና ደላሎችን ጨምሮ እየታፈሱ መሆኑ ታውቆዋል::

በሶስት ምድብ ተከፍለው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ የነበሩት እነ መላኩ ፈንታ የእስረኞች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመምጣቱ የተነሳ ወደ ሰባት ምድብ ተከፍሎ እየተመላለሱ ሲሆን በቀጣይም ሌሎችን ለመያዝ አደኑ እየቀጠለ መሆኑን ከወያኔ ብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ የተገኘው ዜና ይጠቁማል::

በዚሁ በተጀመረው የፍርድ ቤት ውሎ ሰውነቱ ገርጥቶና ከስቶ አንገቱን ቀና ማድረግ ያቃተው መላኩ ፈንታ ያለመከሰስ መብቲ ተገፍፎ ድንገት መያዜ አግባብ አይደለም ብሎ ተናግሮ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ጥያቄዬን አንስቻለሁ ሌሎቹ እንደሆኑት እሆናለሁ ከእንግዲህ አንዳችም ጥያቄ አላነሳም በማለት በመሳወቁ ሌላ ክርክር ሳያስፈልግ ክሱ እንዲቀጥል ተብሎ ለግንቦት 19 ቀጠሮ መሰጠቱ ታውቆዋል::

መላኩ ፋንታ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ሕመም ላይ በመሆኑ መድሀኒት እንዳይገባለት ለይምሰልም ቢሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች በቃል ትእዛዝ ቢሰጡም የቃሊቲ እስር ቤት የበላይ ጠባቂ አብርሀም ወ/አረጋይ የከለከለው መሆኑ ታውቀዋል::

ሰውነቱ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ የቀነሰ ከመሆኑም ባሻገር ገርጥቶና ከንፈሮቹ ደርቀው መናገር እያቃተው በምልክት ብቻ ችሎት ላይ መነጋገር መጀመሩ መላኩ ፈንታ በታሰረበት ጉዳይ ተስፋ ቆርጦ ያለበት ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል ያሉት ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ምክትሉ የህወሀቱ ሰው ገብረዋህድ ግን እንደ ልቡ በችሎቱ እየፈነጨ አንዳንዴም ዳኞቹን እያስፈራራ መታየቱ አስገራሚ ነው ብለዋል::

በመኖሪያ ቤቱ እና በቢሮው ውስጥ በመቶ ሺህ የሚቆጠር የውጭ ሀገር ገንዘቦች እና በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ውስጥ ብር ብሎም የቤት ካርታዎች የተገኘበት እና በእርግጥም ሙስና ውስጥ ተዘፍቆ የተገኘው ይሄው የህወሀቱ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ በችሎት ዳኞቹን እያንጉዋጠጠ እና እያስፈራራ ከመናገሩም ባሻገር በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ በጸዳ ክፍል እና ብዙ እስረኞች ባልበዙበት ክፍል እንዲታሰር መደረጉ አይን ያወጣ መድልኦ እየተፈጸመ መሆኑን ያመላከታል የሚሉ ወገኖች ብዙዎች ናቸው::

የአዲስ አበባ ከተማ የምክር ቤት አባል የሆነውና አሁንም በድጋሚ ተመረጠ ተብሎ በይፋ የተነገረለት የብአዴኑ መላኩ ፈንቲ ያለመከሰስ መብቱ ሳይጠበቅለት ድንገት ከቢሮው ተይዞ ለእስር በመዳረጉ ተበሳጭቶ አቤቱታውን ለችሎቱ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ያለው የፍርድ አሰጣጥ ሁኔታ ፖለቲካዊ መሆኑን ሲረዳ ጥያቄዬን አንስቻለሁ በማለት መልስ መስጠቱን ተከትሎ ክሱ እንዲመሰረትና ቀጥታ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ቀጠሮ መሰጠቱ ታውቆዋል::

መላኩ ቀድሞም ያምመው እንደነበርና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በከባድ ህመም እየተሰቃየ በመሆኑ ልዩ ክትትል ተደርጎለት የተሻለ ህክምና ሳይደረግለት በዚሁ ከቀጠለ በአጭር ግዜ ውስጥ ሕይወቱ ለያልፍ እንደሚችል ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በሚሊዮን የሚቆጠር ብሮችና የቤት መስሪያ ካርታዎች አግበስብሶ በመኖሪያ ቤቱ እና በቢሮው ውስጥ የተገኘበት ገብረዋህድ በበኩሉ ባለቤቲ የታሰረችው አለአግባብ በመሆኑ ትፈታልኝ በማለት

አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ሚስቱ ኮሎኔል ኃይማኖት ተስፋይ ተባባሪው እና የቅርብ አጋሩ እንደሆነች ተነግሮት ጥያቄው ውድቅ እንደተደረገበት ታውቆዋል፡፡

ጉዳዩን ከሚከታተሉ ወገኖች እንደተገኘው ጥቆማ ከሆነ የገብረዋህድ ሚስት ኮሎኔል ኃይማኖት ተስፋይ ከሰራዊቱ በቦርድ እንድትወጣ ተደርጎ እና እህቱዋ ንግስቲ ተስፋይ እንዲሁም የሚስቱ እህት ባል አብረው ሲሰሩ እንደነበርና በተለይ ከአዜብ መስፍን ጋር እጅና ጉዋንት ሆነው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የሚያሳዩ በርካታ ሰነዶች የተገኙባቸው ሲሆን ጉዳዩ ወደ አዜብ ሊያመራ ይሆን ወይ የሚለው ፍርሀትና ስጋት በመርማሪዎቹ ዘንድ እንደደረሰ የሚገልፁ ወገኖች አሉ፡፡

በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ አቅጣጫዎች ከታሰሩት ባለሀብቶች እና ባለስልጣናት ጋር የቀረበ ግንኙነት እና የንግድ ሽርክና እንዳላት የሚገልጽ ማስረጃ ለጸረ ሙስና ኮሚሽን መርማሪዎች የደረሰ በመሆኑ ዘገባው ከተሰራ ስድስት ወራት ባለፈው ዜና ጋዜጠኞችን መክሰሰስዋ የጉዳዩን ትኩረት አቅጣጫ ለማሳት በማሰብ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡

ንብረትነቱ የሼህ መሀመድ አላሙዲን እንደሆነ የሚነገርለት ሰንደቅ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ፍሬው አበበ የተባለው ጋዜጠኛ ባለስልጣናትን ዋቢ አድርጎ አዜብ መስፍን ቤተ መንግስቱን አለቅም ማለትዋን የዘገበው ከስደስት ወራት በፊት የነበረ ቢሆንም አዜብ በአሁኑ ሰዓት እጅግ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባትዋ ለግዜው የትኩረት አቅጣጫ ለማሳት በማሰብ ጋዜጠኛውን ከመክሰስዋም ባሻገር በደህንነት ሰራተኞች ጭምር እያስፈራራችው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

የሼሁ የቅርብ ሰው ...የጋዜጣው የቦርድ ሰብሳቢ...የስፖርት ፌዴሬሽን አመራሩ ተካ አስፋው ላይ ሳይቀር አዜብ ስልክ እየደወለች ያስፈራራች ከመሆንዋም ባሻገር የዜና ሽፋን ለማግኘት ስትል ከላይ እታች እየሮጠች መሆንዋንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን መረጃ ይገልፃል፡፡

አዜብ መስፍን በአሁኑ ሰዓት በእስር ላይ ከሚገኙት ከከተማ ከበደ ጋር ዩዲ ኒሳን ዲዝል ገልባጭ መኪኖችን እያስመጣች ስትሸጥ እንደነበረ..... በዓለም ገና አካባቢ በሚገኝ ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ የአበባ አትክልት ስራ እየሰራች መሆኑን...ከገብረዋህድ እና ከሚስቱ ጋር እንዲሁም ከሎዋቹ እያሱ በርሄ ጋር በመሆን የተከለከለ የቴሌኮሙኒኬሽን ኬብሎችን በምስጢር ያለ ቀረጥ አስገብታ ስትሰራ የነበረ መሆኑን.......ነጋ ገብረእግዚአብሄር ከተባለው በአሁኑ ሰዓት ታስሮ ከሚገኘው የነጻ ትሬዲንግ ባለቤት ጋርም በተለያዩ ግዜ መኪና ያለቀረጥ ክፍያ እያስገባች ስትሸጥ እንደነበረ.....በተለያዩ ዘመዶችዋ ስም ባወጣችው ንግድ ፍቃድ በኮንስትራክሽን ስራ ላይም ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር ሆና እየሰራች ያለች መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃዎች ለጸረ ሙስና መርማሪዎች እጅ እንዲገባ በመደረጉ አሁን በወያኔ ቡድን ውስጥ ምጥ ሆኖ እንደሚገኝ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልፆዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት ተፋፍሞ የነበረው የሙስና ወሬም በአሁኑ ሰዓት የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ስብሰባ የሚደረግበት ወቅት በመሆኑ ወያኔ ገመናው እንዳይጋለጥ አንዳችም ወሬ እንዳይነሳ በመደረጉ ለግዜውም ቢሆን አዜብ መስፍን ፋታ ልታገኝ ችላለች ያሉት ምንጮቹ አንዳንድ አዜብን የማይወዱ

የወያኔ አባላት ጠንክረው ከቀጠሉ መጋለጧ  አይቀሬ ነው ሲሉ ምንጮቹ ግምታቸውን እየሰነዘሩ ይገኛሉ፡፡

አንዳንድ ለህዝብ ተቆርቋሪ እና ሀገር ወዳድ የሆኑ ምሁራኖች በአሁኑ ሰዓት ወያኔ የገዛ ግልገል ባለስልጣናቱን በሙስና አሰርኩ ማለቱን በተመለከተ በጥርጣሬ አይን እያዩት መሆኑን በመግለጽ ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚሁ ምሁራኖች እንደሚሉት ከሆነ ሰሞኑን የጥረግ ዘመቻ የተደረገው በወያኔ ቡድን መሀከል በተፈጠረ ሽኩቻ የተነሳ የአንደኛው ወገን አይሎ በመውጣቱ  የተወሰደ እርምጃ እንጂ በጥናት እና ከልብ ሙስናን ለመዋጋት የተደረገ መስሎ እንደማይታያቸው ገልፀው ይሄንን ለማድረግ ግልጽነት... ተጠያቂነት..... እና የህዝብን መብት ማክበር ሲችሉ ብቻ ነው ሲሉም አስተያየታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡

አክለውም አሁን ጀመርን ያሉት የፀረ ሙስና ዘመቻ እውነት ከሆነ በቀጣይ በዚሁ ጉዳይ የተጨማለቁና የተዘፈቁ ባለስልጣናትን እየመነጠሩ ለህዝብ ይፋ ሊያደርጉ ሲችሉ ብቻ እና ብቻ ነው ካሉ በሁዋላ አሁን በውስጣቸው በተከሰተ የእርስ በርስ ሽኩቻ እና  በተፈጠረ ልዩነት ውጥረቱን ለማርገብ ሲባል ብቻ በወሰዱት እርምጃ ሕዝቡን ለማታለል መሞከራቸው ውጤቱ ኪሳራ ላይ ይጥላቸዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ሰሞኑን በሚቆጣጠሩት ሚዲያዎች በሙስና ታሰሩ ስለተባሉት ባለስልጣናት  ሕዝቡን መቆሚያ መቀመጫ ያሳጡት ወያኔዎች ለአንድ ሳምንት በሚቆየው የአፍሪካ ህብረት 50ኛ ዓመት በዓል ምክንያት አንዳችም ነገር እንዳይነሳ በሚል የተዘጋ ሲሆን ሕዝቡ ግን በዚህም ዙሪያ በቁጭት የሚያነሳቸው አጀንዳዎች መኖራቸው ታውቆዋል፡፡